

# አነስተኛ ንግድ ስራዎች

# የኮሮና ወረርሽኝን ተቋቁመው

## በስራ እንዲዘልቁ የሚረዱ ስልቶች

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከፓን አፍሪካን ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጋር በመተባበር

ሚያዝያ 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ



# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| ክፍል አንድ - ሰራተኞችን ማትጋት | 2 |
| ክፍል ሁለት - የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን (ICT) ጥቅም ላይ ማዋል | 2 |
| ክፍል ሦሥት - የማህበረሰብ እሴትና መልካም ሥነ-ምግባር | 3 |
| ክፍል አራት - ሽያጭን በማሳደግ ኪሳራን ማካካስ | 3 |
| ክፍል አምስት - ቁጠባና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር | 4 |
| ክፍል ስድስት - የሂሳብ አያያዝ፣ ህግና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች | 5 |
| ክፍል ሰባት -የአነስተኛ የግል ድርጅቶች የእርስ በርስ መደጋገፍና ትብብር | 5 |
| ክፍል ስምንት - ወረርሽኙን በአግባቡ መገንዘብና መቆጣጠር | 6 |
| ማጠቃለያ:- | 7 |



# መግቢያ

የኮሮና ቫይረስ በይበልጥ በአነስተኛ የንግድ፣ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች ላይ ጫናውን አበርትቶ በመላው አለም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በማስከተል ላይ የሚገኝ በወረርሽኝ ደረጃ በመሰራጨት ላይ የሚገኝ ተጨባጭ እውነት ነው።

‹‹አነስተኛ ንግድ ስራዎች የኮሮና ወረርሽኝን ተቋቁመው በስራ እንዲዘልቁ የሚረዱ ስልቶች›› በሚል ርእስ የተዘጋጀው ይህምክረ ሀሳብ፤ በደቡብ አፍሪካ ከሚገኙ 27ሺ 439 አነስተኛ የንግድ ስራዎች ባለቤቶችና ስራ ፈጣሪዎች የተሰባሰበ ምክረ ሀሳብን መሰረት በማድረግ የተሰናዳ ነው። ምክረ ሀሳቡን ከእነዚህ አነስተኛ የንግድ፣ የምርትና የአገልግሎት ሰጪ የግል ድርጅቶች ባለቤቶችና ስራ ፈጣሪዎች በማሰባሰብ በመመሪያ መልክ ያዘጋጀው ማርኑስ ብሮድሪክ (Marnus Broodryk) የተባለ የንግድ ስራ ባለሙያና የሂሳብ አያያዝ ድርጅት ባለቤት ሲሆን ‹‹90 መመሪያዎች ለስራ ፈጣሪዎች›› "90 Rules for Entrepreneurs"የሚል ዝናን ያተረፈና በከፍተኛ መጠን የተሸጠ መጽሀፍ ደራሲም ነው።

ማርኑስ ብሮድሪክ ምክረ ሀሳቦቹን ለማሰባሰብ ያነሳሳው በአንዳንድ የንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ እየታየ ያለውን ቸልተኝነት በማስተዋል ነው። ጸሃፊው በሚኖርበት ደቡብ አፍሪካ አንድ የንግዱ ማኅበረሰብ አባል ‹‹ቫይረሱን ችላ ብለን በአወንታዊነት እናስብ - Ignore the virus and think positively!›› የሚል ጽሁፍ የስራ ቦታው ላይ ለጥፎ ማየቱን ይገልጻል።

ይህ ፍጹም አዘናጊ ሀሳብ፤ በርካታ አነስተኛ ንግድ ተቋማት ሰራተኞቻቸውን በትነው እየተዘጉ ባሉበት በዚህ ወቅት መነሳት የሌለበት መሆኑን ብሮድሪክ ጠቅሶ፤ በተለይ አነስተኛ የንግድ፣ የምርትና አገልግሎት ተቋማት የኮሮና ወረርሽኝ የሚያስከትልባቸውን ኪሳራ መቋቋም አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ልዩ ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ያሳስባል።

ትልልቆቹ ኮርፖሬሽኖች በወረርሽኙ ምክንያት የሚከሰተውን ኪሳራ መቋቋም ብቃት እንዳላቸው የሚጠቁመው ባለሙያው አነስተኛ የንግድ፣ የምርትና አገልግሎት ተቋማትን ግን ወረርሽኙ ይበልጥ ሊጎዳቸው እንደሚችል ጠቅሶ የአንድ አነስተኛ ተቋም ከስራ ውጪ መሆን ድምር ውጤቱም አጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ መዳከምን የሚያስከትል መሆኑን ያመለክታል።

የኮረና ቫይረስ (COVID 19) መላውን አለም ባስጨነቀበት በዚህ ወቅት አነስተኛ የንግድ፣ የምርትና አገልግሎት ተቋማት ጫናውን ተቋቁመው እንዲዘልቁ የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ አነስተኛ የግል ስራ ባለቤቶችና ስራ ፈጣሪዎች እንዳሉበት ተጨባጭ እና ነባራዊ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።








# ክፍል አንድ

## ሰራተኞችን ማትጋት

- ሰራተኞች የኮረና ቫይረስ (COVID 19) መጠቃት ስጋት ካደረባቸውየምርመራ ወጪን መሸፈን፤ ውጤቱም ፖዘቲቭ ከሆነአስፈላጊ የጥንቃቄ ርምጃ ለመውሰድ ይረዳዋል፡፡
- ወቅቱ አብዛኛው ሰራተኛ የሚጨነቅበትና የሚፈራበት ጊዜ በመሆኑ የማጽናኛ መልእክት መላክ፡፡
- ሰራተኞች ለምግብ፣ ለመድሀኒትና ለሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች መግዢያ እንዲያውሉት ደሞዛቸውን በቅድሚያ መስጠት፡፡
- በኮሮና ቫይረስ(COVID 19) የተያዙ ሰራተኞችን ልጆች እንዲንከባከቡ ሌሎች ጤነኛ ሰራተኞችን መመደብ፡፡
- ኮሮና ቫይረስ (COVID 19)በሚያደርሰው የኢኮኖሚ ጫና ምክንያት ሰራተኞችን መቀነስ ግዴታ ሆኖ ሲገኝ፤ ሰራተኞች እስከመጨረሻው ከማሰናበትበአነስተኛ ደሞዝ እንዲሰሩ ወይም የግዴታ ፈቃድ እንዲወጡ ማድረግ፡፡ ሰራተኞች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ መርዳት
- በጣም ችግር ውስጥ ላሉ ሰራተኞች የምግብና አስፈላጊ ቁሳቁሶቸ እገዛ ማድረግ

# ክፍል ሁለት

## የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን (ICT) ጥቅም ላይ ማዋል

- በኮሮና (COVID 19)ወረርሽኝ ምክንያት ስራዎችን እንደቀደሞው በገጽ ለገጽ በአካል ተገናኝቶ ማከናወን አዳጋች ስለሚሆን የዕለት ተዕለት የንግድ፣ የምርትና የአገልግሎት ስራዎችን፣
    - በስልክ፣
    - በኢ-ሜል፣
    - በሞባይልአጭር መልእክት
    - በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን (ፌስ ቡክ፣ ቲዊተር፣ ዩቲዩብ፣ ቴሌግራም፣ ስካይፒ፣ የተለያዩ ድረ-ገጾች፣ ወዘተ) በመጠቀም ማከናወን
    - ለተለያዩ ሶፍትዌሮች ጋር የተለማመዱአነስተኛ የንግድ ስራ ባለቤቶችና የግል ደርጅቶች ስራዎቻቸውን ሶፍትዌሮችን ተጠቅመው እንዲያስኬዱ ይመከራሉ፡፡




# ክፍል ሦሥት

## የማህበረሰብ እሴትና መልካም ሥነ-ምግባር

- ማህበረሰቡ ከዚህ ቀደም ተከስተው የነበሩየተለያዩ ወረርሽኞችን በጋራ እንደመከተ ሁሉ የኮሮና ቫይረስን(COVID 19) ስርጭትንምበጋራእንዲከላከልይመከራል
- በችግር ወቅት ባህልንና ማህበራዊ እሴትን አለመዘንጋት
- ችግሮች ሁሌም ቢሆንእድሎችን ይዘው እንደሚመጡ ልብ ማለት
- ከለውጦች ጋር ራስን ማስማማት
- አሁን ከምንጊዜውም በላይ አንዱ ለሌላው የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ እንደመገኘታችን ነባሩን ማህበራዊ ግንኙነት ጥቅም ላይ ማዋል፡፡
- ስራን በእቅድ ማከናወን
- የኮሮና ቫይረስን(COVID 19) አቃሎ አለማየት፤ ከዚያ ይልቅ ችግሩን መጋፈጥና መፍትሄ መሻት
- አንዳችን ለአንዳችን በመቆም በችግር ውስጥ ላሉ መድርስ ይጠበቅብናል የጤና ሚኒስቴርና የአለም የጤና ድርጅት የሚሰጡትን ምክርን ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ማድረግ
- አቅም በፈቀደ ልክለአንዳንድ ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች ድጋፍ ማድረግ

# ክፍል አራት

## ሽያጭን በማሳደግ ኪሳራን ማካካስ

- የዱቤ ሽያጭ አገልግሎት በመስጠት ክፍያውን በሌላ አመቺጊዜ መሰብሰብ
- የተሸጡ ምርቶችን በነጻ ትራንስፖርት አገልግሎትደንበኞችን ዘንድ ማድረስ
- ለኢንተርኔት ተደራሽ ለሆኑና እስካሁን ሽያጭ ላልጀመሩ ነገር ግን የመጀመር እድሉ ላላቸውየኢንተርኔት ሽያጭ መጀመር
- በወርሽኝ ወቅት በርካታ ሰራተኞች ስራ አጥ ሆነው እቤት ስለሚውሉ ስራዎችን በኮሚሽን እንዲሰሩ ማበረታታት
- ሰዎች በወረርሽኙ ምክንያት ቤት ስለሚውሉ ማኅበራዊ ሚዲያና የብሮድካስት መገናኛ ብዙሀንን ይከታተላሉ፡፡ ስለዚህ ምርትና አገልግሎቶችን በነዚህ መገናኛ ብዙን ማስተዋወቅ ውጤታማ ያደርጋል፡፡
- ምርትና አገልግሎትን ለአለም አቀፍ ደንበኞች የሚያቀርቡ ከሆኑ ዋጋ በመቀነስ የሀገር ወስጥ ደንበኞች ግዢ እንዲፈጽሙማድረግ
- ደንበኞችን በተለያዩ ዘዴዎች በመገናኘት ፍላጎታቸውን ማወቅና አዲስ ምርትና አገልግሎት ይፈልጉ እንደሆን ፍላጎታቸውን ማሟላት
- ከ6 እስከ 12 ወራት ለሚሆን ጊዜ ምርትና አገልግሎቶችን ለሚገዙ ደንበኞች የዋጋ ቅናሽ ማድረግ
- ሰፊ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ማከናወንና፤ በተሰማሩበት ዘርፍም አስተዋይ መሪ መሆን





# ክፍል አምስት

## ቁጠባና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር

- የሚሰሩበትን ወይም የሚነግዱበትን ቤት ያከራዮት ሰው የኪራይ ቅናሽ እንዲያደርግሎት ወይም የኪራይ ጭማሪ እንዳያደርግቦት መደራደር
- የቅድሚያ ክፍያ ለሚፈጽሙ ደንበኞች ለቅድመ ክፍያበሚከፍሉት ገንዘብ ላይ ቅናሽ ማድርግ
- ቀድመውክፍያ ለሚፈጽሙ ደንበኞች ክፍያቸውን በካርድ እንዲፈጽሙ መፍቀድ (ጥሬ ገንዘብ እንዲያስገቡ ያለማስገደድ)
- ደንበኛ ከሆኑበትባንክ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብ የሚያገኙበትን ስልት መቀየስ
- ቅድሚያ ክፍያ የማስከፈል አሰራር ካሎት ደንበኞች ቅድሚያ ክፍያውን እንዲፈጽሙማግባባት
- በቁጠባ የተገኘ ገንዘብ በስራ ከተገኘ ገንዘብ እኩል ይቆጠራልና ፧ምርትና አገልግሎት ግዢ ላይ ጠንቃቃ መሆን
- ገንዘብ እንዲቆጥቡ አስተዋጽኦ ላላቸው ሰራተኞች የማትጊያ ጥቅማጥቅሞችንመፍቀድ
- በቅድሚያ የንግድም ሆነ የምርት ስራ ደህንነት እንዲረጋጋና በቂ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት እንዲኖር የሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪና ጉርሻ እንዲዘገይ ማድረግ
- የወጪ መረጃዎችን በመገምግም የተሻለ አማራጭ ካለ መቃኘት
- ወቅታዊ የአሰራር ስርአቶችንና ሂደቶችን በመፈተሸ ውጤታማነታቸውን መገምግም










# ክፍል ስድስት

## የሂሳብ አያያዝ፣ ህግና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች

- የሰራተኛ ቅነሳ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በደንቡ መሰረት መከናወኑን ማረጋገጥ
- ሰራተኞችን በተለየ መንገድ ለማሰራት መላ መዘየድ፡፡ ለምሳሌምበወረርሽኙ ምክንያት ሬስቶራንቶቻችሁ ወይም ሱቆቻችሁ የሚዘጉ ከሆነ፤ ትእዛዞችን በስልክና በማህበራዊ ሚዲያ በመቀበል ሰራተኞች ምግብም ሆነ እቃ ለደንበኞች እንዲያደርሱ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ስራችሁን በአግባቡ ለማከናወን እንድትችሉ ትክክለኛ የሂሳብ መረጃ ማግኘታችሁን ማረጋገጥ
- በተለይ በርካታ የአመት እረፍት ያላቸውን ሰራተኞች የግዴታ ረፍት እንዲወጡ ማድረግ ወጣት ሰራተኞችን የምታሰሩና ለወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ የምትሰጡ ከሆነ የግብር ቅነሳ እንዲደረግላችሁ የሚመለከተውን አካል መጠየቅ
- ከተቻለ የሂሳብ አያያዝ ስራችሁን የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም የሂሳብ ባለሙያዎቻችሁ ከቤት ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ
- አንዳንድ ደንበኞች ስምምነት በፍጥነት ካልተከናወነ ሀሳብ የመቀየርና ክፍያ ላይም ወደ ኋላ የማለት አዝማሚያ ስለሚታይባቸውከደንበኞች ጋር የሚደረግን የስራ ስምምነት በፍጥነት መፈጸም

# ክፍል ሰባት

## የአነስተኛ የግል ድርጅቶች የእርስ በርስ መደጋገፍና ትብብር

- አነስተኛ የንግድ፣ የምርትና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በኮሮና ቫይረስ (COVID 19) ምክንያት የሚደርስባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት በመተባበር መመከት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በንግድና ምርት ሰንሰለት አንዱ አነስተኛ ድርጅት የሌላኛውን አነስተኛ ድርጅት ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚ ስለሚሆን አንዱ ለሌላው የዋጋ ቅናሽ በማድርግ መደጋገፍ ይችላሉ፡፡
- ይህንንም ለማድረግም እርስ በርስ የሚገናኙበት ኔት ወርክ መመስረት ይችላሉ፡፡
- ትስስራቸውን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማጠናከር የኦን ላይን ግንኙነት መመስረትንሊያጠቃልልይችላል፡፡
- በዚህ መነሻም የፈጠሩት ኔትወርክና የኦን ላይን ግንኙነት በቅናሽ የሚያቀርቡትን ምርትና አገልግሎት በማስተዋወቅ ደንበኞችን ለማብዛት ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡




## ክፍል ስምንት

### ወረርሽኙን በአግባቡ መገንዘብና መቆጣጠር

- ለሰራተኞችና ለደንበኞች አገልግሎት የሚውል የእጅ ንጽህና መጠበቂያ (sanitizer) ማዘጋጀት
- ወደ ተለያዩ ስፍራዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን ማቀብ
- ከሰራተኞች፣ ከደንበኞችና ከአቅራቢዎች ጋር የላቀ ተግባቦት መፍጠር
- ወደ ደንበኞችና አቅራቢዎች የሚደረግን ጉብኝት መቀነስና ግንኙነቶችን በስልክ፣ በኢሜልና በስካይፒ ማከናወን
- ሰራተኞች በቤታቸው ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ፤ካልተቻለም በፈረቃ እንዲሰሩ ማድረግ
- ስራዎችን ከቢሮ ውጪ በገላጣ ቦታማከናወን
- ንጹህ አየር እንዲገባ የቢሮ መስኮቶችን መክፈት
- በተቻለ መጠን የእጅ ጓንት፣ የአፍና የአፍንጫ ጭንብልመጠቀም
- የሰራተኞችን እንቅስቃሴ መቆጣጠርና ከማን ጋር እንደተገናኙ ማወቅ ስለማይቻል ሰራተኞች ወደ ስራ ሲገቢ ከተቻለ በኢንፍራ ሬድ ቴርሞሜትር(infrared thermometer) የሰውነታቸውን ሙቀት መጠን በመለካት ወረርሽኙ ከመከሰቱ በፊት ማስቆም







# ማጠቃለያ

የኮረና ቫይረስ (COVID 19)በመላው አለም በወረርሽኝ መልክ እየተዛመተ በመሆኑ ለመንግስታት፣ ለመላው ህዝብና ለግሉ ዘርፍ ስጋት ሆኗል፡፡ በተለይ ጉዳቱ ገቢው ዝቅተኛ በሆነውየህብረተሰብ ክፍልና በአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ላይ ስለሚያይል በአነስተኛ ደረጃ ላይ ያለው የንግዱ ማህበረሰብ ከምንጊዜውም በላይ ተግቶና ተባብሮ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

‹‹ለአነስተኛ ንግድ ስራዎች የኮሮና ወረርሽኝን ተቋቁመው በስራ እንዲዘልቁ የሚረዱ ስልቶች›› በሚል ርእስ የቀረበው ይህምክረ ሀሳብ ከደቡብ አፍሪካ አነስተኛ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትና ስራ ፈጣሪዎች የተሰባሰበ ቢሆንም ለሀገራችን አነስተኛ ንግድ አንቀሳቃሹ ማህበረሰብ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የኢትዮጵያ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽንና ከአሰሪዎች ፌዴሬሽ ጋር በመሆን ሰሞኑን ባወጡት ወቅታዊ መግለጫ የኮሮና ቫይረስ (COVID 19) ባስከተለው ስጋት ምክንያት በሚፈጠረው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት ለሚቀጥለው አንድ አመት፣

- በግል ድርጅቶች የደሞዝ ጭማሪ እንዳይደረግ
- አበልና ጥቅማጥቅም አንዳይኖር
- ሰራተኛና አሰሪዎች ይህን አሰቸጋሪ ወቅት በትብብርና በመደጋገፍ እንዲሻገሩት መግባበት ላይ ተደርሷል፡፡

ማሳሰቢያ፡- የዚህን ምክረ ሀሳብ ዋንኛ ሰነድና ተዛማጅ ሀሳቦች ከ www.marnusbroodryk.com እና instagrame.com/marnusbroodryk ድረ-ገጽና ኢንስታግራም ገጾች ማግኘት ይቻላል፡፡

